# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 14

ሚያዝያ 8 ቀን 2014ዓም (16-04-2022)

ከሁሉ አስቀድሞ ለካቶሊክ እምነት ተከታዮች ሁሉ እንኳን ለብርሃነ ትንሳኤውና ለፋሲካ በዓል አደረሳችሁ እንላለን።

ለዛሬው አገር እንዴት ሰነበተች ዘገባችን ካለፉት ጊዜያቶች ጀምሮ ሲንከባለል መጥቶ አሁን ላይ አፍጦና ገጦ በመታዬት ላይ ያለውን የኦሮሙማው የመስፋፋትና መረን የለቀቀ እብሪት መነሻችን አድርገነዋል።ባለፈው ሳምንት በሸዋ፣በወሎ፣በጎጃም፣በቤንሻንጉል፣በአፋር፣በሲዳማ፣በሶማሊያ የሚያደርገውን የእብድ ውሻ ሩጫ መጥቀሳችን የሚታወቅ ነው።በዛሬውም ሳምንት ውስጥ ካለፈው የተለዬ ባይሆንም የተለያዩት የኦሮሙማ የአነግ ፍልፍል ቡድኖች ተመሳሳይ አቋም ማንጸባረቃቸውን ታዝበናል።በነዚህ በስም እንጂ በዓላማ በማይለያዩት፣በጥቅምና ባስተሳሰብ የተሳሰሩ የአንድ አነግ ውልድ የሆኑ የኦሮሞ ቡድኖች ባስተላለፉት ተመሳሳይ መግለጫና ጫጫታ የእንዶድ ሥሩ አንድ ነው የሚለውን የአበው አባባል በገሃድ ተተርጉሞ አይተንበታል። እንዶድ በአንድ ስር ላይ በቅሎ እንደሃረግ ተያይዞ የሚስፋፋና የሚያድግ፣ትልቅና ትንሽ መጠን ያለው ፍሬ የተሸከመ እጽዋት ነው።ይህ እጽዋት የትም ሆነ በዬትም፣መሬት ለመሬትም ሆነ አጥር ላጥር ቢንሰራፋ የግንዱ መነሻና ስሩ አንድና አንድ ብቻ ነው።ለዚያም ነው የእንዶድ ስሩ አንድ ነው የተባለው።

እንዶድ ለልብስ ጽዳት የሚረዳ አረፋ ባለቤት በመሆኑ የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ ነው።የአነግ ቤተሰብ የሆኑት ቡድኖች ግን በሰው አምሳል የሚንቀሳቀሱ ጉዳት እንጂ ጥቅም የማይሰጡ፣ ሕብረሰብን ካለበት የኑሮ አዘቅት ማላቀቅ ሳይሆን፣በኋላ ቀር አስተሳሰብ የጎሰኝነት መርዝ እዬረጩ ጭራሽ ወደለዬለት የመከራ ዘመን የሚነዱ ፣ እራስ ጠል፣አገራቸውንና ወገናቸውን ለጠላት አሳልፈው የሚሰጡና የጠላት መሣሪያ የሆኑ የጥፋት ሃይሎች መሆናቸው በሚያደርጉት ተግባር ሁሉ የታዬና የታወቀ ነው።ከእንዶድ ጋር የሚያመሳስላቸው አበቃቀላቸው እንጂ ተግባራቸው አይደለም።

ስለትስስራቸው ከሚያሳዬው ብዙ ጽባያቸውና ድርጊታቸው መካከል የሰሞኑ የኦሮሞ ክልል መሪ ነኝ የሚለው የኦህዴዱ ብልጽግና ሽመልስ አብዲሳ ራሱ ያስታጠቀው ወራሪና አሸባሪ ቡድን የሰሜን ሸዋን መሬት ወሮ ሕዝብ ባፈናቀለበት ወንጀሉ ተጠያቂ ላለመሆን የሌባ ዓይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ እንዲሉ ጥፋትና ወንጀሉን በተጠቂው ሰላማዊ ነዋሪ ላይ በተለይም በአማራው ላይ በመደፍደፍና ጽንፈኛ የሚል ቅጥያ በመለጠፍ ከዛም ባለፈ የበቀል እርምጃ እወስዳለሁ የሚል ድንፋታ ማሰማቱ ሲገርም ኦፌኮ የተባለውም ሌላው የአነግ ክንፍ ተመሳሳይ መግለጫ በማውጣት የአማራውን ማህበረሰብ በተለይም ፋኖንና ሚሊሽያውን ለሰላምና ለአንድነት ያልቆመ አክራሪ በማለት ፈርጆ ከኦሕዴድ አቻው ጋር መቆሙን ይፋ አድርጓል።የአነግ ቤተሰቦች የኢትዮጵያ አንድነትን የሚያዩበትና የሚተረጉሙበት መንገድ እነሱ ሥልጣን ላይ እስከተቀመጡ ድረስ እንጂ ከሥልጣን ቢወገዱ ኢትዮጵያም አብራቸው እንደምትወገድ አድርገው ያስባሉ።እራሳቸውን የኢትዮጵያ ዋልታና ምሰሶ አድርገው ይቆጥሩታል።በሕዝብ ትግል ለሥልጣን የበቁና በሕዝብም ትግል ከሥልጣን ሊወገዱ እንደሚችሉ ዘንግተውታል።ያለፉትም ሥርዓቶችና መሪዎች ይሉ የነበረው ይህንኑ ነበር፤ሲወገዱ ግን ኢትዮጵያ ቀጥላለች። በቆዬችበት የብዙ ዘመን ታሪኳ የነበሩት መሪዎች ሁሉም ከነሱ መወገድ በኋላ ኢትዮጵያ ትኖራለች ብለው አያስቡም ነበር።እራሳቸውን የአገሪቱን ህይወት ወሳኝ፣ሰጭና ነሽ አድርገው ይቆጥሩት ነበር፤ያሁኖቹም እንዲሁ።ያሁኖቹን ካለፉት ልዩ የሚያደርገው አገራችንንና ሕዝቧን በጎሳና

በሃይማኖት ለያይተው መግዛታቸው ነው።ያም ቢሆን ለጊዜው ነው እንጂ የቋመጡለት አገር አጥፍቶ የመጥፋቱ ዓላማቸው ሊሳካላቸው አይችልም።ከቀድሞ ጣኦታቸው ከህወሃት ውድቀት ከመማር ይልቅ ህወሃትን መስለውና ተከተው በባሰ ጭካኔ አገርና ሕዝብ እያተራመሱ ይገኛሉ።የአንድነት ሃይሉ ጠንክሮ ከወጣ፣ሕዝቡም ከተተበተበበት የጎሳ ማንነት ሰንሰለት ሲላቀቅ የጎሰኞቹ ዓላማ ይከሽፋል።ለዚያም ነው የአገር ወዳዱ መነቃቃትና መሰባሰብ ብርክና ጭንቀት ለቆባቸው የባጥ የቋጡን የሚቀባጥሩት።

የሥልጣን ወንበሩ በወያኔ ሲውረገረግ ድረሱልኝ ብሎ የተማጸነው መንግሥት ነኝ ባይ ተረኛነት ያሰከረው የኦሮሙማ ቡድን አሁን የተረጋጋ ሲመስለውና ከወያኔም ጋር ለመታረቅ ሽርጉድ ሲል የከፉ ቀን ወዳጁን አሳልፎ ሊሰጠውና ለጭዳ ሊያቀርበው ሲያስብ የአማራውን ልጆች ፋኖንና ሚሊሽያውን በወራሪና አሸባሪ ብሎም በጽንፈኝነት ፈርጆ በመከላከያ ሃይሉ ለማንበርከክ ሲሞክር ማዬቱ ሥርዓቱ ምን ያህል ከሃዲና ጸረ ኢትዮጵያ መሆኑን በግልጽ ያሳያል።በሰሜን ወሎ የመከላከያ ሃይሉን አሰማርቶ ትጥቅ ለማስፈታት ያደረገው ሙከራ ለጊዜው በሕዝቡ ትግል የከሸፈ ቢሆንም አሁንም ቢሆን አማራውን የማጥቃትና የማንበርከክ ሙከራው አልቆመም።ከፋኖና ልዩ ሃይሉ ጋር አብሮ ለመጨፍለቅ ያሰበው ለአማራው የሚቆጬትንና በመሸ ሰዓትም ላይ ቢሆን የመንግሥትን ሴራ ከውስጥ ሆነው ያጋለጡትን የብአዴን ብልጽግና አባላቱንም ጭምር ነው።አቶ ንጉሱ ጥላሁን፣አቶ ፀጋ አራጌና አቶ ዬሃንስ ቧያለው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሕዝባዊነታቸውን በማሳዬታቸውና በብልጽግና ውስጥ የሚካሄደውን ሴራና ሙስና ፣ሌብነት እንዲሁም የፖለቲካ አሻጥር በማጋለጣቸው በአብይ አህመድ መንግሥት ትዕዛዝ ከነበራቸው የአመራር ቦታ ተወግደው የነበራቸውም የደህንነት ጥበቃ ሙብት ተነፍጓቸዋል።የነዚህ ግለሰቦች ጥፋት ሥርዓቱ በተለይም የብአዴን ብልጽግና ሙልጭ ያለ በሌብነት የተካነ ቡድን የሚመራው ድርጅት መሆኑን ፣ለሥልጣን የሚያበቃው መስፈርትም አድር ባይነትና የሌብነት ችሎታ ነው በማለታቸውና ይህንኑም በማስረጃ በማጋለጣቸው ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም የአማራው ማህበረሰብ እነዚህን የቀድሞ ሹማምንት ባለፈው የሥራ ተሳትፏቸው ለጊዜውም ቢሆን ሳያገልና ሳይፈርጃቸው፣አሁን ለሚያሳዩት ሕዝባዊነት ዋጋ ሰጥቶ ይበልጥም ሊጠቀምባቸው እንደሚችል ተረድቶ፣ ከሚደርስባቸው ጥቃት ሊከላከልላቸው ይገባል። አብይ አህመድ ሴረኛና በቀለኛ ስለሆነ ነገ በግለሰቦቹ ላይ ሊያደርስ ያሰበውና የወጠነው ሴራ መኖሩን ከወዲሁ አውቆ ግለሰቦቹን ለመከራ አጋልጦ መስጠት በራስ ላይ መፍረድ ስለሆነ ሕዝቡ ወገንተኝነቱን በተግባር ሊያሳይ ይገባል።ብአዴንም ሆነ አብይ ሊያጠቃ የሚችልበት ቀላሉ መንገድ ከሚቀርባቸው ማህበረሰብ በወጡ ቅጥረኞች ሊሆን ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።የመከፋፈል ሥራ በመካሄድ ላይ ስለሆነ ያንን ክፍተት መድፈኑም አንዱ መፍትሔ ነው።ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባበታል ነውና ያማራው ማህበረሰብ ዙሪያውን ለከበቡት ጠላቶቹ መሣሪያ የሆነውን ጎጠኝነትንና ቡድናዊነትን አሶግዶ በአንድ መቆም ይኖርበታል።ካለፈው ውድቀቱ ሊማር ይገባል።በዬቦታው ተለያይቶ የሚደረገው ትግል ወደ አንድ ማእከል መሰባሰብ አለበት፣በአገር ውስጥ ብቻም ሳይሆን በውጭ አገር በተለያዩ ቦታዎች የሚደረገው እንቅስቃሴና የእርዳታ ዘመቻ በአንድ ጣራ ስር ይሁን የሚለውን ጥሪያችንን አሁንም እንደግማለን።በተበታተነ መልኩ የሚደረገው የግልና የቡድን ጥረት መልካም ቢመስልም ባለፉት ጊዜያቶች እንደታዘብነው ለተቋቋሙበት ዓላማ ሳይሆን ለግለሰቦች ጥቅም መዋላቸው የሚካድ አይደለም።ብዙ ገንዘብም ለተሰበሰበበት ዓላማ ሳይውል የገባበት ሳይታወቅ ቀልጦ ቀርቷል።አለያም ከመንግሥት ጋር ግንኙነትን ለማጥበቅና የሚሹትን ለማግኘት ወይም በጎጠኝነት በከባቢ ጥቅም ላይ እንዲውል ሆኖ ብሔራዊ አንድነታችንን የሚያዳክም እንጂ የሚያጠናክር ተግባር ላይ አልዋለም። ስለሆነም በውጭ የሚኖረው ስርዓቱን የሚቃወም ኢትዮጵያዊ ከዚህ ተደጋጋሚ አሮንቃ ለመውጣትና የተበታተነውን ትግልና ጥረት ወደ አንድ ለማምጣት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲያደረግ ጥሪያችን ነው። ምንም እንኳን በአካል ተገናኝቶ ለመነጋገር ሁኔታው ባይፈቅድም በዘመኑ የመገናኛ አውታር ተገናኝቶ

ለመወያዬት ዕድሉ ሰፊ ነው።ለዚህ ጥሪ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛና ፍላጎት ያላቸው ሁሉ በዚህ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የስነጽሑፍ ክፍል በኩል ሃሳባቸውን ቢያጋሩን መድረኩን ለማመቻቸት እንደሚተባበር ለመግለጽ እንወዳለን።

አድራሻችንም ethioandneteditorial 1@gmail.com

ወደሌላው እርዕስ ስናመራ

ሥርዓቱ የረጨው መርዝ በዬቦታው የሕዝቡን አብሮነት እዬበከለውና እዬሸረሸረው መሆኑን በተደጋጋሚ ገልጸናል።ባሳለፍነው ቀናት በደቡቡ ያገራችን ክፍል በደቡብ ኦሞ በጅንካ ከተማ ተመሳሳይ ውዝግብ ለማዬትና ለመስማት ችለናል።በዚህ ከተማ አካባቢ የሚኖሩ የአራት ወረዳ ነዋሪ ወጣቶች የአሪ ማህበረሰብን ዞን እናደርጋለን በሚል ሰበብ ባነሱት ሁከት እሥርቤት ሰብረው እስረኞችን ለመልቀቅ ሙከራ ከማድረግም አልፈው በነዋሪው ሕዝብ በተለይም በአማራው ተወላጅ ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ለማድረስ ሞክረው ብዙ ሰው መንዳቱ ተሰምቷል።ንብረት ዘርፈዋል አቃጥለዋል። ከመቶ ሃምሳ በላይ የመኖሪያና የንግድ ቤቶች፣ አንድ መስጊድና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ተቃጥለው 900 ቤተሰቦች ባዶ እጃቸውን ሜዳ ላይ ፈሰዋል።ለዓመታት ከሕዝቡ ጋር ተቀላቅለው የኖሩ ነዋሪዎችና ቀሳውስት ለህይወታቸው ስለፈሩ ቦታውን ለቆ ለመውጣት መወሰናቸው ታውቋል።በዚህ የሸብር ተግባር ላይ የከባቢው ፖሊሶችም እንደተካፈሉበት ማስረጃ የወጣ ሲሆን አራት ፖሊሶችም በቁጥጥር ስር ውለዋል ተብሏል።በዚህ ጎሳ ተኮር ጥቃት ቀስቃሽና ተሳታፊነቱ የተነገረው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ታዋቂነት ያተረፈው ሙዚቀኛ ታሪኩ ዲሽታጊና መሆኑ ሲነገር ግለሰቡ ግን ወጣቶቹን እዬለመነና እዬመከረ ወንጀል እንዳይፈጽሙ ከማድረግ በቀር የወንጀሉ ፈጻሚና አስፈጻሚ አይደለሁም ብሏል።ውሸትና ክህደት ባጥለቀለቃት አገራችን የትኛውንም ለማመንና ላለማመን አስቸጋሪ ሆኗል።ይኸው ግለሰብ ከዓመት በፊት በአድዋ በዓል አከባበር የመንግሥት ዝግጅት በነበረበት በመስቀል አደባባይ መድረክ ላይ ወጥቶ ያደረገው ንግግር ከመንግሥት በኩል የተሰጠው ሚሽን ተደርጎ ተቆጥሮ ነበር፤የአሁኑስ የዚያ አካል ላለመሆኑ ምን ማረጋገጫ ይኖራል?ሁሉንም ጊዜ ይፈተዋል። ከብዙ ጥያቄ በኋላ የፌዴራል ሃይል ገብቶ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጁ ሁኔታው የበረደ ቢመስልም የመከላከያ አመራሮች ካላቸው የኦሮሙማ ወገንተኝነትና ተረኝነት ስሜት ብሎም የሰፈነው የጎሳ ስርዓት እስካለ ድረስ ችግሩ ለዘለቄታው አይወገድም፤ጊዜ ጠብቆ የሚያገረሽ ለመሆኑ አያጠራጥርም።ለጊዜው መብረዱ ነዋሪው እንዲያስብና እንዲዘጋጅ ይረደዋል።

በዚሁ የደቡብ ክፍል ነዋሪ የሆኑት ተሰባስበው ወደ ክልሉ መስተዳድር ጽ/ቤት አዋሳ ድረስ በመሄድ መረር ያለ ጥሪና ጥያቄ አቅርበዋል።በሰላም መኖር እንፈልጋለን፣አታፈናቅሉን፣አትከፋፍሉን የሚል የምሬት ቃል አሰምተዋል። ከባለሥልጣኑ በኩል ግን የተሰጠ መልስ የለም።ይህ የሚያሳዬው በሕዝቡ መካከል ምንም አይነት ቅራኔ እንደሌለ፣እንደወትሮው አብሮ በሰላም መኖር እንደሚሻ ሲሆን ለቀውሱ ተጠያቂ የሆነው ሥርዓቱ ከውጭና ከውስጥ መልምሎ የሚልካቸው ቅጥረኛ አሸባሪዎች መሆናቸውን ነው።

ከደቡብ ውጣ ስንል አዲስ አበባ የተበላች ቁብ መሆኗን ያወቅንበት ሰሞን ነበር።

የኦሮሙማው ቡድን በመሪው በሽመልስ አብዲሳ በኩል በአዲስ አበባ ላይ በማካሄድ ላይ ያለውን የመዋጥ እንቅስቃሴ ሂደት መጠናቀቁን ይፋ አድርጓል።እንደ ሽመልስ አባባል አዲስ አበባ እንደ አዳማ የተነጠለ ማንነቷ የተረጋገጠባት፣በስልት ወደ ነባር ማንነቷ ወደ ፊንፊኔነቷ ተመልሳለች የሚል ነው። የኦሮሚያ አስተዳደር ቃል አቀባይ መሥሪያ ቤትም ባወጣው የአንድ ገጽ መግለጫ ላይ ከአስር ጊዜ በላይ ፊንፊኔ በማለት የማረጋገጫ መልእክቱን አስተላልፏል።የአዳነች አቤቤም መስተዳድር በአዲስ

አበባ ውስጥ ሃይማኖት ተኮር የመሬት ዘረፋ እዬተካሄደ ነው በማለት ጣቱን ወደ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቀስሯል።የኦሕዴድ መሪዎች በያቅጣጫው የሚነዙት ወሬ አዲስ አበባ ፊንፊኔ የኛ ናት፣አትንኩብን የሚል ነው።ማንም ይሁን ማንም ሕግና ሥርዓት ሳይከተል የመሬት ወረራ ማካሄዱ ወንጀል መሆኑ አይካድም።አዲስ አበባ የኑዋሪው ሕዝብ ከዚያም አልፎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረት ናት። የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ በመረጠው የከተማ አስተዳደር እውቅናና ፈቃድ የመሬት ባለቤት የመሆን መብት አለው። ማንም እንዳሻው ሊፈነጭበት አይገባም፤ወይም ሥልጣን ላይ ያለ ጉልበተኛ የሚቀራመተውና የሚያዝበት የግል ንብረት አይደለም።

ይህ በእንዲህ እያለ የአሜሪካ ልዩ መልእክተኛ የሆነው ዴቪድ ሳተርፊልድ ከምክትሉ ጋር አዲስ አበባ መግባቱ ታውቋል። ከተሾመ የሦስት ወራት ዕድሜ  ያለው ይህ ዲፕሎማት ከተመደበበት ሥራ ላይ በቀናት ውስጥ እንደሚነሳ ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮ የወጣው ዜና ቢያመለክትም አሁን በመጨረሻ ጉዞው ምን ይዞ መጣ የሚለው ለብዙዎች አነጋጋሪ ሆኗል።የዲፕሎማቱን መምጣት ተከትሎ ወያኔ ሃይሉን ከአፋር አውጥቻለሁ የሚል መግለጫም ማውጣቱ ያለውን መተሳሰር በመጠኑም ቢሆን ያሳያል።በዚህ ላይ አብይ አህመድ የወልቃይትን መሬት አሳልፎ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን ከ5000ሺህ በላይ የደህንነት አባላት ወደ ከባቢው ማሰማራቱ ከአሜሪካኖች ጋር የደረሰበትን ስምምነት ማክበሩን ለማሳዬት እንደሆነ  ሴራውን ከጥርጣሬ ያለፈ አድርጎታል።

የወያኔ ጥቃት ሳይበርድና ከያዛቸው የሰሜን ወሎና የአፋር መሬቶች ሳይለቅ፣ወልቃይትን ለመንጠቅ የሚያደርገውን ወረራ ሳያቆም ፋኖንና የልዩ ሃይሉን አጠፋለሁ ብሎ መዝመት ወያኔ ትግራይን ለመገንጠል ያለውን ፍላጎት ከማገዝ፣  ለኦሮሙማው ቡድንም ወሎንና ጎጃምን ለመዋጥ ላለው ዓላማ መንገድ ከመጥረግ ያለፈ ሌላ ትርጉም የለውም።

የዲፕሎማቱ መምጣት በተጨማሪም አሜሪካኖቹ በሩስያና በኡክሬን መካከል በሚካሄደው ጦርነት ላይ የአፍሪካ አገሮች ጎራ ለይተው ከጎናቸው እንዲቆሙ የመወትወትና የማስገደድ እንቅስቃሴያቸውን በኢትዮጵያ በኩል ለማስፈጸም የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ነው ተብሎ ይገመታል።ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ላይ ሩስያን ወግነው ከቆሙት 24 አገሮች መካከል በመሆኗ  አቋሟን ካልለወጠች የቅጣት እርምጃ ለመውሰድ የታሰበውን ለማስረዳት እንደመጣም የሚናገሩ አልጠፉም።ያም ሆነ ይህ አሜሪካኖች ለኢትዮጵያ ጥቅም ይሠራሉ ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው።ለነሱ ያልወገነ፣በነሱ መዳፍ ሥር ያልሆነ አገር አመድ ቢሆን ይመርጣሉ።የአገር ልዑላዊነት የሚለካው በነሱ ጥቅም ልክ እንጂ በዓለም አቀፍ ሕግና ደንብ አይደለም።ለዚያም ነው ወያኔ የታመነ አገልጋይ ነው ብለው በማሰብ የፖለቲካ፣ የጦርመሣሪያና የዲፕሎማቲክ ድጋፋቸውን የሚያዥጎደጉዱለት።ይህ ማለት የአብይ አህመድ መንግሥት ለነሱ ጥቅም አይቆምም ማለት አይደለም ግን ከወያኔ ጋር ሲነጻጸር ከቻይናና ከሩስያ ጋር ያለው ግንኙነት በመጠንከሩ፣እዚያና እዚህ እዬረገጠ ስላስቸገራቸው፣በሕዝቡ ዘንድ ያለው ተቀባይነት እዬደበዘዘ መምጣቱ፣ከሱ ይልቅ ሌላ ፈረስ አስፈላጊ ሆኖ በማግኘታቸው የሚጫወቱት ጨዋታ መኖሩን ለማሳዬት ነው።

አንዳንድ የዋሆችና የአሜሪካና የምዕራባውያን አሽቃባጮች ለዴሞክራሲና ለሰብአዊ መብት መከበር ከመጣር ባለፈ ኢትዮጵያን የመበደልና የማፈራረስ ፍላጎት የላቸውም ይላሉ።ለነዚህ የምንለው ቢኖር ዩጎዝላቪያ ፣ሊቢያ፣ኢራቅ፣የመን፣ሶማሊያ፣እንዴትና በማን ፈረሱ?ሶሪያንና ኢራንን፣ሩስያንንስ ለመበታተን ማን ጥረት አደረገ?ሩዋንዳውያንንስ ማን በጎሳ ከፋፍሎ አጫረሰ?ከደቡብ አፍሪካው የዘረኞች ስርዓት ጀርባ ማን ቆሞ ነበር?ቅኝ ግዛትና የአሁኑ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የማንስ ውጤት ነው? ለአሜሪካኖቹም ሆነ ለምዕራባውያን ፀሃይ እዬጠለቀች ነው።በአፍሪካ፣በመካከለኛው ምስራቅ፣ በእስያና በደቡብ አሜሪካ ብዙሃኑ ሕዝብ ዓይናችሁ ላፈር ብሏቸዋል፤ተንጠልጥለው የቆሙት

በአምባገነኖችና የጥቅም ተካፋይ በሆኑ አገር በቀል ሌቦች ትከሻ ላይ ነው። እነሱም ይላሉ ቋሚ ወዳጅና ቋሚ ጠላት የለንም!ተጠቅመው መጣል የሚመሩበት ስልት መሆኑን በዚህ ያረጋግጣሉ።

እኛም ይህንኑ አባባል ይዘን ወደ አማራውና የኤርትራ መንግሥት መቀራረብ ስናመራ፣የኤርትራ መንግሥት ለአማራው ልዩ ሃይልና ፋኖ ወታደራዊ ስልጠናና የትጥቅ ድጋፍ ለማድረግ መወሰኑ የሰሞኑ ዜና ነበር።ሻእብያ በኢትዮጵያ ላይ የፈጸመው በደል አሁን ላለችበት ደረጃ ክፍተኛ ድርሻውን መያዙ የሚካድ አይደለም።በጥቅም ግጭት ከወያኔ ጋር ቅርሾ ከገቡ ወዲህ ግን በአካባቢው ደርሶ የማያውቅ እልቂት የተፈጸመበት ጦርነት ካካሄዱበት ከ20 ዓመት ወዲህ በመካከላቸው የነበረው ግንኙነት ሻክሮ ሲንከባለል ቆይቶ ከ 16 ወር በፊት በወያኔ ተንኳሽነት በተጀመረው የእርስ በርስ ውጊያ ሻእብያ ጣልቃ በመግባት ትግራይን በመውረር ድጋፍ አይሉት በቀል ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በማበር እብሪተኛውን ቡድን ድባቅ ለመምታት በመቻላቸው በሁለቱ አገሮች የነበረው የጠላትነት መንፈስ ለመቀዬር ተችሏል።ይህ የመቀራረብ ዝንባሌ፣በአብይና በኢሳያስ መካከል የአባትና የልጅ ፍቅር እስኪመስል ድረስ ተወድሶ የነበረ ሲሆን በዘላቂነት ግን ሊቀጥል አልቻለም።በአብይ አህመድ ከህደት ለአሜሪካኖችና ለወያኔ ባሳዩው መቀራረብና ለፍላጎታችው አጎብዳጅነት የሻእብያን መሪ በቅጡ እንዳስኮረፈው የግንኙነታቸው መቀዛቀዝ ያሳያል።በተለይም የአብይ አህመድ ፓርቲ የብልጽግናን ማሸነፍ ተከትሎ በተዘጋጀው ድግስ ላይ እንዲሁም በአፍሪካ ሕብረት ጉባኤ ስብሰባ ላይ የኢሳያስ አፈወርቂ አለመገኘት ለዚህ ማሳያ ነው።በዛፍ ተከላ ላይ አንለያይም ያሉ ሰዎች በነዚህ አገራዊና አህጉራዊ ትልቅ መድረኮች ላይ አብሮ አለመታዬት ከሌላ አንጻር የሚታይ አይሆንም። በቅጡ ተኮራርፈዋል።በኩርፊያም ብቻ አልቆመም  ወያኔና የኦሮሙማው ቡድን በአማራው ላይ የሚፈጽመውን በደል እንደ ምክንያት በመውሰድ ኢሳያስ ለመበቀል ሲል  ከአማራው ማህበረሰብ ጋር ግንኙነት ለማጠንከር እንደወሰነ የሚሰሙት ግምቶች ሚዛን ይደፋሉ።

ይህ መቀራረብ ለአማራው ይዞለት የሚመጣው ዘላቂ የሆነ መልካም ነገር መኖሩ ቢያጠራጥርም ካለው ሁኔታ ስንነሳ በጠላቶች ጎራ የሚፈጠርን ልዩነት ተጠቅሞ የራስን ፍላጎት ማስከበር ብልህነት እንጂ ከድክመት ሊቆጠር አይችልም።እንደ ድክመት የሚቆጠረው የራስን ሁለመና፣ጓዳና ጎተራ ከፋፍቶ ከሰጡ፣ምስጢርን ዘክዝኮ ካካፈሉ፣ በኢሳያስ ፍላጎትና ትእዛዝ ስር  ከወደቁ ነው።ፋኖም ሆነ ልዩ ሃይሉ የአመራር ማእከሉን ከራሱ መሬት ውጭ መትከል አይኖርበትም።ምንም እንኳን አማራው ችሎታ ያላቸው የጦር አሰልጣኞች እንዳሉት ቢታመንም የኤርትራም አሰልጣኞች የወያኔንና የኦነግን ውስጣዊ ወታደራዊ የመዋጋት ችሎታና ወታደራዊ ባሕል ስለሚያውቁት ያንን እያካፈሉ በአማራው መሬት መጥተው እንዲያሰለጥኑ ስምምነት ማድረጉ መልካም ነው።ያልጠረጠረ ተመነጠረ ነውና የዛሬው ወዳጅነት ለነገው ባላጋራነት ወይም የጥቅም ግጭት አጋልጦ እንዳይሰጥ ከወያኔና ከሻእብያ፣ከሻእብያና ከኦሕዴድ/ኦነግ  በጠላትነት ከተጠናቀቀው የሞቀ ፍቅር ትምህርት መቅሰም ይገባል።ግንኙነቱና መቀራረቡ ግልጽና መርህ የተከተለ ፣ለወደፊቱም የጠና መሠረት የሚጥል ቢሆን ለኤርትራም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የወደፊት ኑሮና መቀራረብ አስተማማኝ ቁልፍ ይሆናል።ኢትዮጵያ ከኤርትራ ፣ ኤርትራም ከኢትዮጵያ የሚፈልጉት የጋራ ጥቅም አላቸው።ከሚለያያቸው ይልቅ የሚያቀራርባቸው ይበዛል።ያንን በጨዋና በታሪካዊው ግንኙነታቸው አንጻር ተሳስበው ቢረዳዱ አሁን ካሉበት ችግር መውጫ መንገድ ይሆናቸዋል።ከውጭም ተጽእኖና ጫና ለመላቀቅ የሁለቱ አገር ሕዝቦች መቀራረብ ወሳኝ ነው።

ለአማራው አስተማማኝ አጋር በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምነው የሌላው ማህበረሰብ ተወላጅ የሆነው ዜጋ ነው።በውሸት ትርክት ናላው የዞረውና ለጥፋት የተሰለፈውን መንጋ ገርቶ ለመመለስ የሚችሉትን የራሱን ጎሳ ተወላጆች በመቅረብ አገር ለማፈራረስ የተነሳውን ቡድን አብሮ እንዲታገል ለማድረግ

የሚያስችል ሥራ ቢሰራ የተሻለ ነው።ሕዝብ ለሕዝብ የሚቀራረብበትን መድረክ መፍጠር የሁሉም ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያዊ ተግባር ነው።

በሳምንቱ መገባደጃ ላይ የተሰማው ሌላው አነጋጋሪ ጉዳይ አብይ አህመድ የጦር አበጋዞቹን ሰብስቦ አራምባና ቆቦ የሆነ ንግግር ማድረጉ ነው።በዚህ ንግግሩ እንደተለመደው የሁሉም ዘርፍ ሊቅና ብቸኛ አዋቂ ሆኖ ለመተንተን ያደረገው ሙከራ ይበልጥ ጤነኛነቱን ጥያቄ ውስጥ ከቶታል።ሰሞኑን ወታደራዊ ልብስ ለብሶ መከረሙና ስብሰባውንም በወታደራዊ ልብስ መምራቱ ለዬትኛው ዘመቻ ተሰናዳ የሚል ጥያቄ ጭሯል።ከአምስት ወራት በፊትም መሔዴ ነው ዘመቻ ባለበት ወቅት በዚሁ አለባበስ ቀርቦ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም።ምንም እንኳን አራምባና ቆቦ ቢሆንም የስብሰባው ይዘት ሲጨመቅ አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶና የተሸረበበት አደጋ አስጨንቆት ወታደራዊ ክንፉ እንዳይከዳው አድኑኝ የሚል ጥሪ ያቀረበበት ምልጃ ሆኖ ታይቷል።

በጎሳ ተዋረድና አውጫጭኝ የተሰለፈውን የመከላከያ ተቋም ከጎሳ እይታና አስተሳሰብ መራቅ አለበት ሲል መከላከያውም ሆነ ጠቅላላው ያገሪቱ ተቋም የሚመራበት የብሔር ብሔረሰቦች በሚል ጥላ ስር የሚተገበር የጎሳ ሕገ መንግሥት መኖሩን የዘነጋው ይመስላል።የሰበሰባቸውን የጦር መኮንኖች አታስታውሱም ብሎ ሲተቻቸው እሱ እራሱ የቆመበት ሕገመንግሥትና ሥርዓት የጎሳ መሆኑን አላስታወሰም፣እረስቶታል።በሌላም መልኩ ወታደራዊው ክንፍ ሥልጣኑን እንዲረከብ ያመላከተበት ስብሰባ መስሏል።ሌሎቹ ነጥቀው ከሚያዋርዱት ወታደሩ ቢይዝ እራሱን በዋና አዛዥነቱ ቦታ አድናለሁ ብሎ ያሰበም ይመስላል።ይህ ሁሉ ሲደመርና ሲቀነስ የስብሰባውን ምክንያት ለማወቅ እሩቅ መሄድ ወይም ውስብስብ የሂሳብ መሣሪያ መፈለግ አያሻም።የመወገድ ስጋት እንዳለበት ያሳያል።

አደጋው ከዬት በኩል ሊመጣ እንደሚችልም ሲሰላ ከዚያው ከኦሮሙማው ጎራ ሊሆን እንደሚችል የገጠጡ ፍንጮች ያስረዳሉ።የኦፌኮ፣የኦነግ፣የኦሕዴድ፣የሌሎቹም አናሳ ጎሳ ተቃዋሚዎች እንዲሁም የአማራው ብልጽግና ውዝግብ፣የሶማሌውና የደቡቡ ብልጽግና ውጥረት፣የአፋሩ ማንገራገር ፣የኑሮ ውድነቱና የሕዝቡ እሮሮ ለአብይ ብልጽግና ቡድን መፈራረስ መንገድ ጠራጊ ሆኗል።የአሜሪካኖች በፍቅረ ወያኔ ማበድ፣የተለያዩ ኤጀንሲዎች መተባበር፣የጁዋር ሞሃመድ የኢትዮጵያ ዜግነት መረጋገጥና የፓስፖርት ባለቤት መሆን የተጠነሰሰውን የመንግሥት ግልበጣ ሴራ መኖሩን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

ወታደሩን በሰበሰበ ማግስት አብይ አህመድ ወደ አማራው መኖሪያ ሸዋሮቢትና ወልቃይት መሄዱም ተሰምቷል።እዚያ የሄደበት ምክንያቱ የአማራውን መነሳሳትና ቀና ቀና ማለቱን አይቶ ለመደለል መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው። በአንድ በኩል ትጥቁን ለማስፈታት የመከላከያውንና የደህንነቱን ብዙ ሠራዊት ልኮበት፣እራሱ የሚመራው የኦሕዴድ /ኦነግ ቡድን የከተተ አዋጅ አውጆበት ባለበት ሰዓት ያንን ለማድበስበስ እራሱ በቦታው መገኘቱ ሌላ ተልእኮ በራሱ ለሚመራው ለነገው የኦሕዴድ /ኦነግ ወረራ መንገድ ጠራጊ ለመሆን ነው። ሊያሶግደው የሚፈልገውን የኦሕዴድ /ኦነግ ሌላኛው ቡድን ለመምታት የአማራውን ድጋፍ ለማግኘትም ነው የሚሉ አልጠፉም።ያም ሆነ ይህ አማራው በያዘው መንገድ ተደራጅቶ ከተጠናከረ ከራሱ አልፎ ለኢትዮጵያ ብሎም ለምስራቅ አፍሪካ አይበገሬነት ዋና ደጀን እንደሚሆን ያውቁታል።ስለሆነም ኢትዮጵያን ለመከፋፈል ለሚሞኙ የጎሳ ቡድኖችና የውጭ ሃይሎች በጠላትነት ፈርጀውታል።ቢቻል በሰላም አለያም በሃይል ሊደመሰስ የተፈረደበት አገር ወዳድ ስለሆነ ከሁሉም ወጥመዶች እራሱን ማዳን አለበት።ሊድን የሚችለውም በያዘው መንገድ ሲገፋበት ብቻ ነው።አገር ወዳዱ ሁሉ ከአማራው ጎን ሊሰለፍ ይገባል።የሚያደርገው ትግል ለራሱ ብቻ ሳይሆን የግፍ ሰለባ ለሆኑት ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ጭምር ነው።የሁሉም አገርና ቤት ለሆነችው ኢትዮጵያ ህልውናና ልዑላዊነት ነው።

ለአማራውም ሆነ ለጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለው አንዱና ብቸኛው መዳኛ መንገድ በአንድ አገር አቀፍ ንቅናቄ ሥር ተሰልፎ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ነው።የሽግግር መንግሥቱም በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ጽኑ አቋም ያለው፣በዳር ድንበሯ የማይደራደር፣የጎሳ ፖለቲካና የክልል አወቃቀርን የሚጠዩፍ፣ የሃይማኖት ወገንተኝነት የሌለው፣በኢትዮጵያ የዘመናት የነጻነት ታሪክ የሚኮራ፣ ለዴሞክራሲና ለፍትሕ መሰፈን የሚታገልና በተግባር የሚገልጽ፣የውጭ ሃይሎች ባሪያና ተላላኪ ያልሆነ፣ብሔራዊ ክብሩንና ጥቅሙን አሳልፎ የማይሰጥ መሆን ይኖርበታል።ዳግም የጎሰኞችና የወታደሮች አምባገነን መንግሥት እንዳይመጣ በሩን በህብረት ጠንካራ መዝጊያ ሊዘጋው ይገባል። የጎሰኞቹ መገለባበጥ፣አብይ በጁዋር ቢቀየር፣ወይም የወያኔ ና አጋሮቹ መመለስ ለከፋ ስቃይ እንጂ ለተሻለ ለውጥ አይዳርጉትም።

ኢትዮጵያ ከጎሳና ከሃይማኖት በላይ ናት!በነጻነትና በአንድነት ለዘለዓለም ትኑር!!